በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ. 210328

ህዳር 28 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች-** ሳንቴ የህክምና ማዕከል-- ጠበቃ ዜና ደባሉ ቀርበዋል

**ተጠሪ-** ወ/ሮ ህይወት ጌትነት - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የስራ ስንብትን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረውም በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ በቀን 04/03/2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በፋርማሲስት የስራ መደብ ላይ ከቀን 11/04/2011 ዓ.ም ጀምሮ በወር ብር 11,200.00 እየተከፈለኝ እስከ ቀን 30/12/2012 ዓ.ም ድረስ ሳገለግል ብቆይም አመልካች በወቅቱ በነበረው የኮቪድ 19 ወረርሺኝ ምክንያት ያለማስጠንቀቂያ እና ካሳ የስራ ውሌን አቋርጦታል፡፡ ስለሆነም ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ተብሎ የስራ ስንብት ክፍያ፣ የሁለት ወር የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የስድስት ወር ደሞዝ ካሳ፣ ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት የሶስት ወር ደሞዝ፣ የ2011 ዓ.ም የ14 ቀን እና የ2012 ዓ.ም የ15 ቀን የዓመት እረፍት በገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በበኩሉ በሰጠው መልስ የተጠሪን ደመወዝ፣ የቅጥር ዘመን እና የስራ መደብ ያመነ ሲሆን ስንብቱን በሚመለከት ተጠሪ እንደሚሉት የስራ ውላቸው የተቋረጠው በህገ-ወጥ መንገድ ሳይሆን ለገሃር አካባቢ ይገኝ የነበረው የአመልካች የጤና ማዕከል አካባቢው ለልማት በመፈለጉ ምክንያት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እንዲፈርስ ሲደረግ በርካታ ሰራተኞች ተሰናብተዋል፤ ተጠሪ ስራ እንዳይፈቱ በሚል ምክያት በተቋሙ ስር በሚተዳደረው ሳንቴ ዲያግኖስቲክ ላባራቶሪ ተዘዋውረው በፋርማሲ ግምጃ ቤት ውስጥ እንዲሰሩ ተደርጓል፤ ይሁን እንጂ ተጠሪ ያሳዩት የስራ ውጤት  እና መሻሻል አጥጋቢ ስላልነበረ ከአስተዳደር ኃላፊው ጋር ተነጋግረው የስራ ውላቸው እንዲቋረጥ የተስማሙ፣ ክፍያን በሚመለከት ክሊራንስ ካዞሩ በኋላ በህጉ መሠረት እንደሚከፈላቸው ተገልፆላቸው ማስፈረም ጀምረው የአስተዳደር ውሳኔ እና ፎርማ ሲቀራቸው ያቆሙ በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው፤ የዓመት እረፍት ክፍያን በሚመለከት ተጠሪ ያላቸውን ጊዜ ተጠቅመው ጨርሰው ተጨማሪ የ8.5 ቀን እረፍት የተጠቀሙ በመሆኑ እንዲያውም ለአመልካች ብር 3,173.33 ሊከፍሉ ስለሚገባ ይህኑ ገንዘብ ይክፈሉ ተብሎ ይወሰንልን፤ የምስክር ወረቀትን በመተመለከተ ደግሞ ለመስጠት ዝግጁ ነን በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ምን እንኳን አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለን የስራ ውል ግንኙነት በስምነት የተቋረጠ ነው ቢልም ይህንኑ የሚያሳይ ማስረጃ ያላቀረበ ከመሆኑ በላይ የስራ ውሉ በተቋረጠበት ወቅት የኮቪድ 19 ወረርሺኝን ለመከላከል በወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012 እና ደንብ ቁጥር 446/2012 አንቀጽ 33(9) መሠረት የስራ ውልን ማቋረጥ በተከለከለበት ጊዜ በመሆኑ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው፤ አመልካች ለተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያ፣ የሁለት ወር የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የስድስት ወር ደሞዝ ካሳ በጠቅላላው ብር 103,156.00 እንዲከፍልና የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ፤ የዓመት እረፍት ክፍያን እና ለገዘየ ክፍያ ቅጣት እንከፈላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ በሚመለከት ደግሞ ተጠሪ ያልተጠቀሙት ጊዜ ስለመኖሩ በማስረጃ ያረጋገጡ እና ክፍያው የዘገየውም ክሊራንስ አዙረው ያልጨረሱ በመሆኑ ስለሆነ ሊከፈላቸው የሚገባ ክፍያ የለም፤ እንዲሁም አመልካች ተጠሪዋ ካላቸው የዓመት እረፍት ዉጪ የተጠቀሙ በመሆኑ የተጠቀሙበት ጊዜ በገንዘብ ተቀይሮ ይክፈሉኝ ሲል ያቀረበውን ጥያቄ በዚህ መዝገብ የሚስተናገድ አይደለም በማለት ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኘው አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ይግባኙ ተሠርዞበታል፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በቀን 30/10/2013 ዓ.ም በተፃፈ 03 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመዋል ያላቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙለት ጠይቋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገውን መግባባት እና የአሰሪና ሰራተኛ አዋጁን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ፤ አመልካች በስራ አጋጣሚ ያጎደሉትን ንብረት ቀርበው መተማመኛ እንዲሰጡ ተጠይቀው እምቢተኛ ሆነው እያለ፤ እንዲሁም ተጠሪ ስንብቱ የተደረገበትን የቃል ስምምነት በመቀበል ለተግባራዊነቱም ክሊራንስ ማዞር መጀመራቸው የስራ ውሉ ተቋርጦ ጥቅማጥቅም ለመስጠት የነበረውን መግባባት የሚያሳይ ሆኖ እያለ ስምምት ስለመኖሩ የሚያሳይ ማስረጃ የለም ተብሎ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው መባሉ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረበውን እና ተጠሪ የስራ ውላቸውን ያቋረጡት በስምምነት መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ የስር ፍርድ ቤቶች ከተቀበሉት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኋላ ማስረጃውን ያለፉበት፣ ስምምነት አይደለም፣ ስንብቱም ህገ-ወጥ ነው ያሉበት አግባብነት ተጠሪ ባሉበት መጣራት አለበት በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪ በቀን 28/11/2013 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኞችንን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍ ባለመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቶ ተከራክሯል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ከተያዘው ጭብጥ፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት በኮቪድ ወረርሽኝ ወቅት ሠራተኛን ከስራ ማሰናበት የሚከለክለዉን ህግ በመተላለፍ አመልካች የወሰደባቸዉ የስራ ማሰናበት እርምጃ ህገ ወጥ መሆኑን ሲሆን፣ አመልካች በሰጠዉ መልስ የስራ ዉሉ መቋረጡን ሳይክድ ሊቋረጥ የቻለዉ ለገሐር የነበረዉ የአመልካች የጤና ማዕከል በልማት ምክንያት በመፍረሱ ብዙ ሠራተኞችን ያሰናበተ ሲሆን ተጠሪ ስራ እንዳይፈቱ በማሰብ በጤና ማዕከሉ ስር በሚተዳደረዉ ሳንቴ ዲያጎኖስትክ ላብራቶሪ በመድሃኒት ሻጭነት የመደባቸዉ ቢሆንም የስራ አፈፃፀማቸዉ አጥጋቢ ባለመሆኑ ከአስተዳደሩ ጋር ዉይይት ተደርጎ ዉሉ በስምምነት ነዉ በማለት ይከራከራል፡፡

የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ይህንኑ በጭብጥነት በመያዝ አመልካች የስራ ዉሉ የተቋረጠዉ በስምምነት ነዉ በማለት የሚከራከር ቢሆንም በህግ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 25 መሠረት በጽሑፍ የተደረገ ስምምነት መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ አለመቅረቡን፣ አመልካች ተጠሪ በተመደቡበት ስራ ያሳዩት አፈፃፀም አጥጋቢ መሆኑን ገልፆ የሚከራከር ቢሆንም ይህን የሚያሳይ ማስረጃ አለመቅረቡን ከድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ አዋጅ ቁጥር 1156 ከአንቀጽ 23 ጀምሮ ባሉት አንቀጾቹ የስራ ዉል የሚቋረጥባቸዉን ሁኔታዎች የሚደነግግ ሲሆን፣ የተቋረጠዉ የስራ ዉል ህጋዊ መሆን ያለመሆኑ አጣርቶ በመወሰን ረገድ የስራ ዉሉ የተቋረጠበት ምክንያት እንደየጉዳዩ ባህርይ በእነዚህ ድንጋጌዎች ላይ ከተመለከቱት ሁኔታዎች አንፃር መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ፣ ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ፣ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉ ተጠሪ በተመደቡበት ስራ ያሳዩት አፈፃጸም አጥጋቢ ባለመሆኑ ዉይይት ተደርጎ ዉሉ በስምምነት የተቋረጠ መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 25 (2) ላይ ከተመለከተዉ ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የስራ ዉልን በስምምነት ማቋረጥ ህጋዊ ዉጤት የሚኖረዉ ስምምነቱ በጽሑፍ የተደረገ ሲሆን ነዉ፡፡ አመልካች በጽሑፍ የተደረገ ስምምነት ያላቀረበ ስለመሆኑ ማስረጃን መዝኖ ፍሬ ነገርን ለማጣራት ስልጣን ባለዉ በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ከላይ እንደተመለከተዉ ተጠሪ በተመደቡበት ስራ ያሳዩት አፈፃፀም አጥጋቢ አለመሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አመልካች አለማቅረቡ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በእርግጥም የስራ አፈፃፀማቸዉ አጥጋቢ አለመሆኑ እንደነገሩ ሁኔታ በአዋጁ አንቀጽ 27(1/ሠ) ወይም በአንቀጽ 28(1/ሀ) መሠረት አመልካች በእራሱ አነሳሽነት ዉሉን ማቋረጥ እንዲችል ምክንያት ሊሆን ይችላል፤ ከዚህ ዉጭ ዉሉን ለማቋረጥ ተጠሪ መስማማታቸዉን የሚያሳይ በጽሑፍ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የተደረገ ስምምነት ባልቀረበበት ሁኔታ የተጠሪ ስራ አፈፃፀም አጥጋቢ የነበረ መሆን ያለመሆኑ እንዲሁም ተጠሪ ክሊራንስ ያዙሩ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ተይዞ ሊመረመር የሚገባዉ ነጥብ አይደለም፡፡ አመልካች እንደሚለዉ ተጠሪ ያጎደሉት መድሃኒት መኖሩ እና የክሊራንስ ሂደት ማጠናቀቅ አለማጠናቀቃቸዉ በጽሑፍ ያልተደረገን ስምምነት ህጋዊ የማድረግ ዉጤት ስለማይኖረዉ አመልካች በዚህ ረገድ የሚያነሳዉም ክርክር ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ የስራ ዉል የሚቋረጥበትን አግባብ በተመለከተ አዋጁ የተለያዩ ምክንያቶችን የሚደነግግ ሲሆን አመልካች የስራ ዉሉ የተቋረጠዉ በህጋዊ መንገድ ነዉ በማለት የሚከራከረዉ ዉሉ በስምምነት የተቋረጠ መሆኑን በመጥቀስ ሆኖ ነገር ግን ስምምነቱ በጽሑፍ የተደረገ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ያላቀረበ ከመሆኑ አንፃር ሲታይ የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስንብቱ ህጋዊ ነዉ በሚል መወሰኑም ሆነ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ይህንኑ በትዕዛዝ በማጽናቱ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁጥር 80236 ላይ የካቲት 15 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፣ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 250562 ላይ ግንቦት 26 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንተዋል፡፡
2. የሰበር አጣሪ ችሎት ሐምሌ 02 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

ማ/አ　　　　　　　　　　　　　የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም